# የመላው ኢትዮጵያውያን ተስፋ!

**ክፍል አንድ**

**ከተስፋዬ ለማ**

**03/28/14**

የተጨበጠ ተስፋ፤ ኢትዮጵያውያን ገንዘባቸውን፣ ጉልበታቸውንና እውቀታቸውን በማስተባበር እውን እያደረጉት ያለ ታላቁ የህዳሴ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ግድብ ሦስተኛ ዓመቱን አስቆጠረ። በያዝነው መጋቢት ወር ይህንኑ ለማብሰርና እስካሁን በግንባታው ሂደት የተመዘገቡ ለውጦችን ለመገንዘብ በዓሉ በተለያዩ ዝግጅቶች እየተከበረ ይገኛል። መጋቢት 24 ቀን 2006 ዓ.ም ለኢትዮጵያ ህዝብ ስላለው አጠቃላይ ሁኔታና ቀጣይ እንቅስቃሴን በሚያፋጥን መልክ የሚያስፈልገውን ለይቶ በማቅረብ በዓሉ ይጠቃለላል ተብሎ ይጠበቃል።

ዓባይ ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለቀጠናው ህዝቦች ከድህነት ለመውጣት ለሚያደርጉት ጥረት ወሣኝ ሚና የሚኖረው የተፈጥሮ ሃብት ነው። ሆኖም ላለፉት ዘመናት ኢትዮጵያውያን ተጠቃሚ ሳይሆኑ ዘልቀዋል። ይልቁን ዓባይ የዘመናት የህዝብ ቁጭትና እንጉርጉሮ ሆኖ ቀርቶ ነበር። በዓባይ ውኃ ልማት የማይታሰብ ተደርጎ መደምደሙም የማይረሳ ጉዳይ ነው።

የኢትዮጵያን ህዝብ ዓባይን ከሚያህል ትልቅ የተፈጥሮ ፀጋ ተጠቃሚ ባለመሆኑ የተነሳ ለዘመናት በእያንዳንዱ ዜጋ ሲብሰለሰል የኖረው ቁጭት ብቻ ነበር። አሁን ያ ቁጭት መቋጫውን አግኝቷል። ዓባይ ከዚህ በኋላ የቁጭት እንጉርጉሮ የሚሆንበት ዘመን ገሃድ ሆኗል። ዓባይ ዳቦ መሆን ሊጀምር ነው።

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዝብ በታላቅ ተስፋ ላይ ይገኛል። ለዘመናት ሲንጠው የኖረውን ድህነት ለማራገፍ በአንድነት ደፋ ቀና በማለት ላይ ይገኛል። ከድህነት የመውጣት ተስፋው ለምልሟል። ለዚህ ደግሞ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ የበኩሉን ድርሻ እየተወጣ ይገኛል። ዓባይ የሀገር ሲሳይ፤ ዘላቂ የልማት መሠረት መሆኑ የግድ ሆኗል።

ይህንን የተፈጥሮ ሃብት በተለይ ለኤሌክትሪክ ማመንጫነት መጠቀም የጎላ ጠቀሜታ አለው። እንደሚታወቀው የኤሌክትሪክ ኃይል ለአንድ አገር እድገት መሠረት ነው። ኢትዮጵያ ባለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት እያስመዘገበች የመጣችው ፈጣን የምጣኔ ሀብት እድገት ከኃይል ማመንጫ ውጭ የሚታሰብ አልነበረም። መሠረታዊ የእድገት ለውጥ ሊመጣ የሚችለው በቂ የኃይል ምንጭ ካለ ብቻ ነው።

አገሪቱ ባለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት መጠነ ሰፊ  የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ግድቦች ግንባታ አካሂዳለች። የተከዜ፣ የፊንጫ፣ የግልገል ጊቤ፣ የጣና በለስና ሌሎች ከፍተኛ ወጪ የጠየቁ የኃይል ማመንጫ ግድቦች ተገንብተዋል። የነበራትን ዝቅተኛ የኃይል መጠን ማሳደግ በመቻሏ በአገሪቱ ኢንቨስትመንት እየተስፋፋ መጥቷል። የኢንዱስትሪ ልማቱም በዚያን ልክ እያደገ መጥቷል።

ይህ አገሪቱ ለተለያዩ የኃይል ማመንጫዎች ግንባታ ከሌሎች የልማት ሥራዎች ጋር ጎን ለጎን አጣጥማ መስራት በመቻሏ ምክንያት የመጣ ነገር ነው።  ከውኃ ከሚገነቡት የኤሌክትሪክ ግድቦች በተጨማሪ አገሪቱ የንፋስና የሶላር የኤሌክትሪክ ምንጮችንም በማምረት ላይ ትገኛለች።

ይህንኑ የተገነዘበው የኢትዮጵያ ህዝብና መንግሥት የኃይል ምንጭ ግድቦቹን የበለጠ በማጠናከር ላይ ይገኛል። አዳዲስ ግድቦችን የመገንባት ሥራው  በአምስት ዓመቱ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ልዩ ትኩረት ካገኘው አንዱ ዐቢይ የልማት ዘርፍ  ነው። በዘርፉ በእቅድ ተይዘው እየተሰሩ ካሉ ግድቦች መካከል የአንበሳውን ድርሻ የያዘው ደግሞ  ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ነው።

ታለቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ  የመላው ኢትዮጵያውያን ብሩህ ተስፋ ነው። አገሪቱ በዓባይ ወንዝ ላይ መገንባት ከምትችላቸው ልማቶች ሁሉ በግዙፍነቱም ሆነ በጠቀሜታው የጎላ ድርሻ ያለው ግድብ ነው። የህዳሴው ግድብ አገሪቱ ከድህነት ለመላቀቅ የምታደርገውን ጉዞ ለማሳካት የሚኖረው አስተዋጽኦ ተኪ አይኖረውም።

ለአገሪቱ ምጣኔ ሀብት እድገት የሚኖረው ድርሻ እጅግ የጎላ በመሆኑ ግብጻውያኑና አንዳንድ የኢትዮጵያ መልማትን የማይፈልጉ ግለሰቦች የግድቡን ጉዳት ያሉትን እየለቃቀሙ ከማስተጋባት ወደ ኋላ አላሉም። ላለፉት ሦስት ተከታታይ ዓመታት ካናፈሷቸው ነገሮች አንዱ አገሪቱ ካላት የአቅም ማነስ የተነሳ ፕሮጀክቱ በፋይናንስና በእውቀት ማነስ ምክንያት ይቋረጣል፤ እውን አይሆንም የሚል ነበር።

ታላቁ የህዳሴ ግድብ መቋረጥ ይቅርና ለአፍታ እንኳን ሊዘገይ የማይችል የኢትዮጵያውያን እስትንፋስ መሆኑን የተገነዘበው የኢትዮጵያ ህዝብና መንግሥት ለዚሁ ስኬት ያላሳለሰ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል። በአገሪቱ በሙሉ አቅም እየተገነባ ያለው ይህ ግድብ ከመጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ እስካሁን ድረስ ባለው ጊዜ በተደረገው የግንባታ ሂደት እስከ 27 ቢሊዮን ብር ወጪ ተደርጎለታል። ከ30 በመቶ በላይ የሚሆነው ግንባታም ተጠናቋል። ከሦስት ዓመታት በፊት በወርሃ መጋቢት የፈነጠቀው ጮራ፣ የተጠነሰሰው ተስፋ እነሆ ፍሬ እያፈራ ይገኛል።

የታላቁ የህዳሴው ግድብ ግንባታ በላቀ ደረጃ ላይ በሚገኝበት በአሁኑ ወቅትም ቢሆን የግብጽ ፖለቲከኞችና የኢትዮጵያ ጠላቶች ያለውን ግስጋሴ ለማደናቀፍ በዲፕሎማሲ፣ በፕሮፖጋንዳና በሌላም አማራጭ እየተጠቀሙ ይገኛሉ።

የግብጽ ፖለቲከኞችና አንዳንድ የኢትዮጵያ ጠላቶች የግድቡ የመሠረት ድንጋይ ከተጣለበት እለት ጀምሮ እስካሁን ድረስ ግንባታውን ለማሰናከል ካልሆነ ደግሞ ለማጓተት ይጠቅም ይሆናል ያሉትን ማንኛውንም አማራጭ በተለያየ መንገድ ለማስፈፀም ሲንቀሳቀሱ ቆይተዋል፤ አሁንም በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ።

የተለያዩ የሚዲያ አውታሮችን በመጠቀምም ቅስቀሳ አድርገዋል። የግድቡን ጠቀሜታ እንዳይታይ ለማድረግም ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላል በሚል ሰርተዋል። መጀመሪያ የአካባቢውን ሥነ ህይወት ያውካል፣ የተፋሰሱ የታችኛው አገራት የሆኑት የሱዳንና የግብጽን ህዝብ ይጎዳል በሚል በከፍተኛ ደረጃ አስተጋብተዋል።

ይህ ጥረታቸው የኢትዮጵያውያንን የልማት ተስፋ ለማጨለምና የልማት እንቅስቃሴ ለመግታት አልመው ከተነሱ የኢትዮጵያ ጠላቶች ጋር በመተባበር በሰፊው ዘምተውበታል። ይህ የህዳሴው ግድብ ይፋ ከሆነበት ዕለት ጀምሮ የተሰራ ሥራ ግብጻዊያን አሁንም ቢሆን ይህንን ከመፈፀም አልተቆጠቡም። እያካሄዱት ያለው ፕሮፖጋንዳ ውጤት አልባ መሆኑን እየተረዱትም ቢሆን ከዝምታ መናገርና ጥቂት ሰዎችንም ቢሆን ማደናገር ይሻላል በሚል ብሂል ቀጥለውበታል።

ይህንን ከግብጽ ተቀብለው በከፍተኛ ደረጃ እያራገቡ የሚገኙ በአገር ውስጥና በውጭ አገራት የሚገኙ አንዳንድ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች አመራሮች ናቸው። የግብጻዊያኑ ዘመቻም ከዚሁ ጋር ተጣጥሞ ላፍታም አልቆመም። አሁንም ቀጥሏል። ግድቡ በእቅዱ መሠረት እንዳይከናወንም የቻሉትን ያህል ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ። ኢትዮጵያውያንን ለዚሁ ተግባራቸው ማሰለፋቸው ሌላም የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት ነን ተብዬዎች ገበና ይፋ ያወጣ ጉዳይ ሆኗል።

ግብጻዊያን ማንኛውንም ዓይነት አማራጭ እንጠቀማለን ሲሉም ይደመጣሉ። ከመጀመሪያውም ቢሆን ማንኛውንም የሚያዋጣቸውን አማራጮችን ከመጠቀም ወደ ኋላ ያሉበት ወቅት የለም። ያዋጣናል ካሏቸው አማራጮች አንዱም የዓባይ ተፋሰስ አገራትንና ሌሎች ተጽዕኖ ያሳድራሉ ያሏቸውን አገራት በሙሉ ማግባባትና ለኢትዮጵያ ድጋፍ እንዳያደርጉ ተጽዕኖ ማሳደር ነበር። ይህ በታላቁ ህዳሴ ግድብ የሚያመጣው ተጽዕኖ ባለመኖሩ አሁን ደግሞ የጦርነት አማራጭ የሚል በተለያዩ ሚዲያዎች መዘገባቸው አልቀረም።

የኢትዮጵያ መንግሥት በበኩሉ ይህንን የተሳሳተ በልማት ላይ የሚካሄድ ዘመቻን ለመቀልበስ የቻለውን ያህል የዲፕሎማሲ ጥረቶችን አድርጓል። ከዚህ የተነሳም በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውን ጊዜና ቦታ ሳይገድባቸው ለተቀረው ዓለም ትክክለኛ መረጃ በመስጠት በኩል የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ በማድረግ ግብጽ በጭፍን እየዘረጋች የምትገኘውን የሃሰት ዘመቻ ማክሸፍ ተችሏል። በአሁኑ ወቅት የህዳሴው ግድብ ጉዳት አለው ብለው ከሚያምኑት ይልቅ ለቀጠናው የኢኮኖሚ ትስስርና ሠላም ወሣኝ ሚና አለው የሚሉት ሚዛን

እየደፉ መጥቷል። በዚህ ምክንያትም የግብጽና የአንዳንድ የግብጽ ቡችላ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች አመራሮች እያደረጉ ያሉት ፍትሃዊነት የሌለው ጭፍን የዲፕሎማሲ ጥረት የሚያመጣው ምንም ዓይነት ለውጥ እንደሌለ መገንዘብ አያዳግትም።

መንግሥት፣ ኃላፊነት የሚሰማቸው የአገር ውስጥና የውጭ ሚዲያ ተቋማት እንዲሁም ዲያስፖራው በአገር ውስጥ በተለያየ ሙያ የተሰማራው ህዝብ የታላቁ የሕዳሴ ግድብን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ለዓለም ኅብረተሰብና ለተፋሰሱ አገራት ትክክለኛውን ሁኔታ ለማሳየት የተሰራው ሥራ ውጤታማ ሆኗል። ለዚህ ማሳያው ደግሞ የተፋሰሱ አገራት ለታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታ ያላቸው አዎንታዊ ፖለቲካዊ ድጋፍ አንዱ ነው።

የግብፅ መንግሥት በግድቡ ዙሪያ መነጋገር ካስፈለገው ከሌላ ሀገር መንግሥት ጋር ሳይሆን፤ ከኢትዮጵያ መንግሥትና ህዝብ ጋር መሆን እንደሚገባው እየታወቀ በህዝቦች መደናገርን ለመፍጠር ወደተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት ጉዳዩን እወስዳለሁ በማለት ማደናገሩን ተከትሎ በአገር ውስጥም ሆነ በዓለም አገራት የተለያዩ መድረኮችን በማዘጋጀት በተካሄዱ ፕሮግራሞች የህዳሴው ግድብ እውነታን የማሳወቅ ተግባራት በኢትዮጵያውያን ምሁራንና ከፍተኛ ባለሥልጣናት የተካሄዱባቸው ሁኔታዎች ነበሩ። በዚሁ ሂደትም እንደዚህ ዓይነት ጉዳይ የሚመለከት ዓለም አቀፍ ሕግ እንደሌለ በሕዝቡ ዘንድ ግንዛቤ እንዲፈጠር አስችሏል።

ለግብጽ መንግሥትና ህዝብ ጠቃሚው ነገር ሌላ ጎታች ሃሳብ ከማምጣት ይልቅ በዓለም አቀፉ የባለሙያዎች ቡድን የቀረበውን ሃሳብን መቀበልና መተግበር ነው። ዝክረ ሃሳቡን ወደ ተግባር ለማሸጋገር ከታላቁ የህዳሴ ግድብ ጋር ተያይዞ የቀረበውን ጥናት ወደ ኋላ ለመጎተትና የግብጽ ሕዝብ ተጎጂ እንደሆነ አስመስሎ ማቅረብ ተገቢ አልነበረም። ግድቡ በግብጽና በሱዳን ሕዝቦች ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ ተጽዕኖ አለመኖሩ በአጥኚ ቡድኑ ሪፖርት ላይ የተቀመጠ በመሆኑ የዓለም አቀፍ የባለሙያዎች ቡድን በድጋሚ እንዲቋቋም መጠየቅ የማያስፈልግ ጉዳይ

ነው። ግብጽ ይህንን ሃሳብ ታቅርብ እንጂ በሱዳንም ሆነ በኢትዮጵያ በኩል ጭራሽ ተቀባይነት የሌለው መሆኑ በይፋ ተገልጿል።

አዲስ ዓለም አቀፍ የባለሙያዎች ቡድን ማቋቋም ለምን አስፈለገ? ግብጽ ይህንን አዲስ ቡድን ማቋቋም የፈለገችው ቀደም ሲል ጥናት አድርጎ ሪፖርት ባቀረበው ዓለም አቀፍ ቡድን ከቀረበው መደምደሚያና ዝክረ ምክር የተለየ ነገር ይፈጠራል በሚል እንዳልሆነ እሙን ነው። ጥናቱ በበቂ ሁኔታ ሣይንሳዊ መንገድ ተከትሎ ተከናውኗል።

ግድቡ በግብጽም ሆነ በሱዳን ህዝቦች ላይ የሚያደርሰው የጎላ ችግር እንደማይኖርም በግልጽ አስቀምጧል። የግድቡ ግንባታም ቢሆን ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ እንደሆነ ተሰምሮበታል። ግብጽ የቀረበውን ሪፖርት ላለመቀበሏ በቂ ምክንያት የላትም። በመሆኑም ምክንያቷ የህዳሴው ግድብ ጉዳይ ሳይሆን ሌላ ቀጠናዊ ሥጋት እያደረባት መምጣቱ ሊሆን ይችላል የሚሉ የፖለቲካ ተንታኞች አሉ። ኢትዮጵያ በዚህ መልክ እያደገች የምትሄድ ከሆነች በቀጠናው የሚኖራት ተጽዕኖ በከፍተኛ ደረጃ ያድጋል። ከህዳሴው ግንባታ መጠናቀቅ በኋላ ደግሞ የአገሪቱ ምጣኔ ሀብት የበለጠ ይወነጨፋል።

የግብጽ ፖለቲከኞች የህዳሴው ግድብ ይጎዳናል በሚል እምነት ሳይሆን ኢትዮጵያ አደገች በሚል የቅናት ወላፈን በመለብለባቸው ነው የተለያየ የማይጨበጥ ሃሳብ እያመጡ ኅብረተሰቡን እያደናገሩ ያሉት። ያም ሆኖ ይህ ግን እያደረጉ ያለው የዲፕሎማሲ ጥረት ከንቱ ነው። የከሸፈ ዲፕሎማሲ እንደሆነ ለማንም ህቡዕ አይደለም።

ግብጽ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን ለማሰናከል የጦርነት አማራጭ ትጠቀማለች የሚለው የማደናገሪያ ሃሳብ መሰማት ከጀመረ ወራትን ብሎም ዓመታትን አስቆጥሯል። አገሪቱ በኢትዮጵያ ላይ የመጨረሻው አማራጭ ያለችውን ጦርነት ልትከፍት እንደምትችል በተለያዩ ሚዲያዎቿ በኩል በማስተጋባት ላይ ትገኛለች።

በእርግጥ ግብጾች ይህንን አያስቡም ብሎ መደምደም አይቻልም። ሆኖም ግን ግብጽ ኢትዮጵያ ላይ ጦርነትን ለማወጅ በሚያስችል ተጨባጭ ሁኔታ ላይ መሆኗንና አለመሆኗን መገንዘብ የግድ ይላል። አገሪቱ በአሁኑ ወቅት ያለችበት ሁኔታ ብቻ ሳይሆን ከባቢያዊ ሁኔታውስ ምን ይመስላል? የሚለውን መረዳት በግብጽ ፕሮፖጋንዳ ከመደናገር ያድን ይሆናል።

በአሁኑ ወቅት በሃገረ ግብጽ ውጥረት ነግሷል። ህዝቡ በአራት ጎራዎች ተከፍሏል። አንዱ ጽንፈኛው የሙስሊም ወንድማማቾች ቡድን ነው። ሁለተኛው ደግሞ እነዚህን ቡድኖች የሚፃረረውና በግብጽ ከኃይማኖት አክራሪነት የፀዳ መንግሥት እንዲቋቋም የሚፈልገው ቡድን ነው። ሦስተኛው ቡድን ወታደራዊ ክንፉና ደጋፊዎቹ ናቸው። ሌላው ጎራ ደግሞ የቀድሞ የግብጽ ፕሬዚዳንት የሆስኒ ሙባረክ አቀንቃኞችን የያዘው ቡድን መሆኑ ይታወቃል። አራቱ ቡድኖች አገሪቱን አራቱ ማዕዘናት ጫፍ ላይ ይዘው ይጎትቷታል። አገሪቱ ተወጥራ ትገኛለች። ኃይማኖታዊ ጽንፈኝነት ነግሶባታል። እነዚህ የማይታረቁ ቡድኖች የበላይነትን ለመያዝ የሚያደርጉት ትግል ለሁከትና አለመረጋጋት ዳርጓታል።

በግብፅ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በተካሄደ ሕዝባዊ ምርጫ ፕሬዚዳንት ሆነው የተመረጡት ፕሬዚዳንት መሐመድ ሙርሲ፣ በሆስኒ ሙባረክ ዘመን የጦር ኃይሉ ጠቅላይ ኤታ ማዦር ሹም ሆነው ሲሰሩ የነበሩትን ጄኔራል መሐመድ ሁሴን ታንታዊን ከኃላፊነት በማንሳት፣ አብዱል ፈታህ አል ሲሲ በጄኔራልነት የሾሚቸው ቢሆንም ህዝቡ ፕሬዚዳንት መሐመድ ሙርሲ ከሥልጣን እንዲወርዱ በሠላማዊ ሠልፍ በመጠየቁ የተነሳ ወታደራዊ ክንፉ እኚህን ሰው ከሥልጣን አስወግዷል። ጄኔራል አብዱል ፈታህ አል ሲሲም ወደ ሥልጣን ያመጧቸውን ፕሬዚዳንት ሙርሲን ከሥልጣን በማውረድ በእርሳቸው መሪነት ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደርን መሥርተዋል፡፡

አንዳንድ ተንታኞች እንደሚሉት የፊልድ ማርሻልነት ማዕረግን በቅርቡ ያገኙት አል ሲሲ የዓባይን ፖለቲካ ከግብፅና ከኢትዮጵያ በማሻገር የዓረብ አገሮችና የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች አጀንዳ እንዲሆን ለማድረግ እያጣሩ መሆኑን ነው። ለዚህ

ድምዳሜ እየተሰጠ ያለው ትንተና መሠረቱ የፊልድ ማርሻሉ የፖለቲካዊ አካሄድ እንደሆነ በርካቶች ይናገራሉ፡፡

የዓረብ አገሮችን በመያዝ ጠንካራ ፖለቲካዊ ጫና አሳድራለሁ የሚል እምነት ይዘው እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ። በዚህ ምክንያትም እንደገና ሌላ ዓለም አቀፍ የባለሙያዎች ቡድን እንዲቋቋም መምረጣቸው ይታወቃል። ዋናው ዓላማ በዚህ ቡድን ወዳጅ አገራት ያሏቸውን የዓረብ አገራት ባለሙያዎች እንዲሳተፉና ለማድረግ በማሰብ እንደሆነም ምንጮች ይጠቁማሉ። ሰውየው አዲስ ቡድን ካልተመሰረተ ከኢትዮጵያ ጋር መግባባት አይቻልም የሚል መደምደሚያ ሲሰጡም ተደምጠዋል።

የጦርነት ምርጫ ሳይቀር ሁሉንም አማራጭ እንጠቀማለን በማለት የግብጽን ህዝብ የሚያታልሉት እኚህ ሰው ለመሆኑ ኢትዮጵያን በጦርነት ለማንበርከክ የሚያስተማምን ምን ኃይል አላቸው ተብሎ ሲታይ ግን አንድን ተራራን ከሥፍራው ነቅሎ ወደ ሌላ ሥፍራ የመውሰድ ያህል ነው።

በውጥረትና በሁከት የተሞላ የውስጥ ሠላምና መረጋጋት የሌለበት አገር ተይዞ የሌላ አገር ህዝቦችን ልማት ለማደናቀፍ ጦር እመዛለሁ በሚል የሚነፋው ጡሩምባ ከባዶ ጮኸት ያለፈ አይደለም። ምናልባትም ጦርነቱ ከቅዥትና ከህልም የዘለለ እንደማይሆን በርካታ የፖለቲካ ተንታኞች ይናገራሉ።

እስካሁን በነበረው ሂደት የግብጽ መንግሥትና የነሱን ሃሳብ አራጋቢዎች ያሰቡት የተሳካ አይመስልም። በዲፕሎማሲው መንገድ የሄዱት ርቀትም ከመክሸፍ የታደገው ነገር የለም።

ዓለምን ቢያካልሉ የተፋሰሱ አገራትን ቢማጠኑ ኢትዮጵያ እያካሄደች ያለው ልማት ፍትሃዊ በመሆኑ ሃሳባቸው ተቀባይነትን አላገኘም። ጦርነት የሚባለውም ከህልምና ከምኞት የዘለለ አይሆንም። በዚህ ሁኔታ የህዳሴው ግድብ ባለፉት ሦስት ዓመታት መጠናቀቅ የሚገባውን ያህል ተጠናቋል። በቀጣይ ዓመትም የመጀመሪያ ምርቱን ያቋድሰናል።

የሚያዋጣው አብሮ መሥራትና በጋራ ተጠቃሚ መሆን ነው። በዓባይ ወንዝ በሚገነባው የህዳሴው ግድብና ሌሎች መጠነኛና ከፍተኛ የኃይል ማመንጫና የመስኖ ሥራዎች ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ የቀጣይ በርካታ ዓመታት የልማትና የእድገት ተስፋ ሆነው እንደሚዘልቁ ምሁራን ይተነብያሉ።